የሱፐርኢንቴንዷንት የማህበረሰብ ተሳትፎ ተከታታይ መርሃ-ግብር

ከማህበረሰባችን የሰማናቸው ዋና ዋና ነጥቦች

ሱፐርኢንቴንዷንት ቤን ሹልዲነር ከየካቲት እስከ ሚያዝያ 2026 ባለው ጊዜ ውስጥ፣በሰባቱም የቦርድ ዳይሬክተር ዲስትሪክቶች እና በአንድ የኢንተርኔት ስብሰባ ላይ ባደረጓቸው ስብሰባዎች ከ1,000 በላይ የሚሆኑ ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች፣ሰራተኞች እና የማህበረሰብ አባላት ተሳትፈዋል።

ተሳታፊዎች በጥሩ ሁኔታ እየሄዱ ናቸው ያሏቸው ጉዳዮች

ብቁ እና ተንከባካቢ መምህራንና ሰራተኞች

መምህራን፣አማካሪዎች፣ርዕሰ መምህራን እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች፤ለተማሪዎች ስኬትና መልካም ግንኙነት በትጋት የሚሰሩ፣አሳቢ እና ለስራቸው ታማኝ መሆናቸው በውይይቱ ላይ ተገልጿል።

አዎንታዊ የትምህርት ቤት ድባብ/ማህበረሰብ

ቤተሰቦች ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችና ቤተሰቦች የትምህርት ቤቱ አካል እንደሆኑ እንዲሰማቸው ፣እንዲሁም ለባህል ስብጥርና ለወላጆች ተሳትፎ የሚሰጡት ትኩረት በመልካም ጎኑ ተጠቅሷል።

ተጨማሪ የትምህርት ማበልጸጊያ እና ከትምህርት ሰዓት ውጭ የሚሰጡ እድሎች/አማራጮች

ሙዚቃ፣ስነ-ጥበብ፣የአካል ብቃት እንቅስቃሴ (PE)፣ቴአትር፣ሳይንስና ቴክኖሎጂ (STEM)፣ከትምህርት ሰዓት በኋላ የሚሰጡ ፕሮግራሞች፣ስፖርት እና ባህላዊ ዝግጅቶች፤ለአንድ ተማሪ ሁለንተናዊ እድገት (Whole Child) አስፈላጊ እንደሆኑ ይታመናል።

ሁለት ቋንቋዎችን እና ዘርፈ-ብዙ ቋንቋዎችን መሰረት ያደረጉ የትምህርት ፕሮግራሞች

ሁለት ቋንቋዎችን መሰረት ያደረጉ ትምህርቶች የማህበረሰቡ ኩራት ከመሆናቸውም በላይ ቤተሰቦች ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን እንዲመርጡ የሚያበረታታ ዋና ምክንያት እንደሆነ ተገልጸዋል።በመሆኑም እነዚህ ፕሮግራሞች በበለጠ ሁኔታ ተጠናክረው እንዲቀጥሉና ተደራሽነታቸው እንዲሰፋ ጥያቄ ቀርቧል።

የማህበራዊና ስሜታዊ ትምህርት (SEL) እና የተማሪዎች ድጋፍ

የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች እና ማህበራዊና ስሜታዊ ክህሎትን የሚያሳድጉ ስራዎች ለተማሪዎች ደህንነት ያላቸው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ በውይይቱ ወቅት ተገልጿል።

በትምህርት ቤት ደረጃ የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ

መምህራንና ርዕሰ መምህራን ከቤተሰቦች ጋር የሚያደርጉት መደበኛና ግልጽ ግንኙነት፣እንዲሁም በየሳምንቱ በሱፐርኢንቴንዷንቱ የሚላኩ ኢሜይሎች አድናቆት ተችሯቸዋል።

መሠረታዊ ፍላጎቶችን ማግኘት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ድጋፎች

በትምህርት ቤት የሚቀርቡ ነፃ የቁርስ እና ምሳ አገልግሎቶች እንዲሁም የጤናና የቤተሰብ ድጋፍ አጋርነቶች፤ ለለተማሪዎችና ለቤተሰቦች ወሳኝ ድጋፎች እንደሆኑ ተገልጸዋል።

አካዳሚክ (የትምህርት) ዕድሎች

ቤተሰቦች ለከፍተኛ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች፣ የተፋጠነ የሂሳብ ትምህርት እና በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ መሆን የጀመረው የንባብ ሳይንስ እያሳየ ያለውን አዎንታዊ ውጤት በከፍተኛ ሁኔታ አድንቋል።

ተሳታፊዎች በጥሩ ሁኔታ እየሄዱ አይደሉም ያሏቸው ጉዳዮች

የበጀት፣የሰው ኃይል እና የተማሪዎች ምዝገባ አለመረጋጋት

ቤተሰቦች ግልጽ ያልሆነ የበጀት አጠቃቀም፣የመማሪያ ክፍሎች መጨናነቅ፣የሰራተኞች እጥረት እና በጥቅምት ወር የሚደረጉ የሰራተኞች ሽግሽጎች የተማሪዎችን የመማር ሂደት የሚያውኩና ፍትሃዊነት የጎደላቸው መሆናቸውን ገልጸዋል።

የመረጃ ልውውጥ፣ግልጽነት እና እምነት

ብዙ ቤተሰቦች ከዲስትሪክቱ በሚወጡ ወጥ ያልሆኑ መልእክቶች፣ተደጋጋሚ ለውጦች እና ግልጽነት በሌላቸው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች የተነሳ ያላቸውን ቅሬታ ገልጸዋል።

የከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ትምህርት እና አካዳሚያዊ ጥራት

አገልግሎቶች ወጥነት የሌላቸው መሆኑ፣የተማሪዎችን የተለያየ የመማር አቅም ግምት ውስጥ ያስገባ የትምህርት አሰጣጥ ውስንነት እና የትምህርቱ ጥራት (ፈታኝነት) እየቀነሰ መምጣቱ በቤተሰቦች ዘንድ እንደ ስጋት ተነስተዋል።

ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች እና ድጋፎች

የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና የ504 አገልግሎቶች ወጥ ያልሆኑና ለመረዳት አስቸጋሪ እንደሆኑ ተገልጸዋል፤በተጨማሪም የሰው ኃይል እጥረት እና ግልጽ ያልሆነ ተጠያቂነት እንደሚታይባቸው ተጠቅሷል።

ቴክኖሎጂን ከልክ ያለፈ መጠቀም

ተማሪዎች ለረጅም ሰዓት በዲጂታል መሣሪያዎች ፊት ማሳለፋቸው፣ በተለይም በታችኛው ክፍሎች ያለው ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑ ተገልጿል።በተጨማሪም የሞባይል ስልክ እና የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ (AI) አጠቃቀምን ስመልክቶ ግልጽ መመሪያዎች አለመኖር በብዙዎች ዘንድ እንደ ስጋት ተነስቷል።

የትምህርት ቤት ደህንነት እና አካባቢያዊ ሁኔታ

ቤተሰቦች የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎች ወጥነት የሌላቸው መሆኑ፣የተማሪዎች የባሕሪ ችግር እየተባባሰ መምጣቱ እና ስለ አካላዊ ደህንነት ስጋቶችን ጠቅሰዋል።

ፍትሃዊነት እና የግብዓት አቅርቦት አለመመጣጠን

ፍትሃዊነት እንደ ትልቅ ግብ ቢቀመጥም፣በተግባር ግን በሁሉም ትምህርት ቤቶች እኩል ተፈጻሚ እየሆነ እንዳልሆነ ይስተዋላል።

የበጎ ፈቃደኞችን እና የቤተሰብ ተሳትፎን የሚገቱ መሰናክሎች

የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ለመስጠት የሚጠየቁ መስፈርቶች አሰልቺና ግልጽነት የጎደላቸው መሆኑ ተገልጿል፣እና ቤተሰቦች ብዙውን ጊዜ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ተሳትፎ እንደሚደረግ ይሰማቸዋል።

ተሳታፊዎች ለማሻሻያ ያቀረቧቸው ሃሳቦች:

- የበጀት ግልጽነትን ማሳደግ እና ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን ማረጋገጥ
- የሰራተኞችን ሁኔታ ማረጋጋት እና በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት መሰረታዊ አገልግሎቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ
- የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን ማሻሻል እና ማንኛቸውም ውሳኔዎች ከመተላለፋቸው በፊት ቤተሰቦች ቀድመው እንዲሳተፉና ሃሳብ እንዲሰጡበት ማድረግ።
- የአካዳሚክ ጥራትን ማጠናከር፣በክህሎት ላይ የተመሰረተ የማስተማር ዘዴን መከተል እና የከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን የትምህርት ዕድሎችን ማመቻቸት
- የሁለትዮሽ ቋንቋ (Dual Language) ትምህርት ፕሮግራሞች ማጠናከርና ይበልጥ ተደራሽ እንዲሆኑ ማስፋፋት
- ከፍተኛ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን መገደብ እና ግልጽ የአጠቃቀም ደንቦችን ማስቀመጥ
- የበጎ ፈቃደኝነት እና የወላጆች ተሳትፎ አሰራሮችን ቀላል እና ተደራሽ ማድረግ
- ግልጽና ተጠያቂነት የሰፈነበት የመሠረተ-ልማቶች እና የትምህርት ቤቶች መልሶ ማደራጀት እቅድ ማውጣት

ቀጣይ እርምጃዎች:

ሱፐርኢንቴንዴንት ሹልዲነር ይህንን አስተያየት ዲስትሪክቱን ለመምራት ለሚወስዳቸው የአጭርና የረጅም ጊዜ እርምጃዎች እንደ መመሪያ ይጠቀምበታል።በየወሩ የሚካሄዱ የማህበረሰብ ተሳትፎ መድረኮችን ለመቀጠል ያቀደ ሲሆን፣ይህም በተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮች እና በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች (አንደኛ ደረጃ፣መካከለኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ) ላይ የሚያተኩሩ ውይይቶችን ያካትታል።ስለ ስብሰባዎቹ የሚሰጡ አስተያየቶችም በጊዜ ሂደት የውይይቶቹን ቅርጽና ይዘት ለማሻሻል ጥቅም ላይ ይውላሉ።ለሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ለምታደርጉት ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እናመሰግናለን።

የስብሰባዎቹ ማጠቃለያ:

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ድረ-ገጽ (URL) ይጎብኙ ወይም የQR ኮዱን ስካን ያድርጉ:

https://www.seattleschools.org/what-we-heard/